ይህ ፀረ-መድልዎ ፖሊሲ: በዚህ በሚመለከተው ርዕስ ላይ፤ የተማሪዎች ከዚህ ቀደም በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና/ወይም መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

**ቻንስለሩ ያጸደቁት:** ______________________

**በስራ ላይ የዋለበት ቀን:** ኦክቶበር (October) 1 ቀን 2021

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# ፀረ-መድልዎ ፖሊሲ: ተማሪዎች

## I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን (SCOPE)

ሁሉም ተማሪ የመወደድ ስሜት እንዲሰማው፣ ችግርን ተቋቋሚነት ስሜት እንዲኖረው እና በአዎንታዊነት ተጽዕኖ የሚያደርግ ማህበረሰብ እንዲሆን ለማዘጋጀት እና ጠንካራና ሁሉን አካታች የሆነ የመማሪያ አካባቢዎችን ለሁሉም ተማሪዎች በመስጠት በሕይወታቸው እንዲበለጽጉ መደረጉን ለማረጋገጥ፤ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) በቁርጠኝነት ይሰራል።

ይህን የቃል-መግባት ቁርጠኝነትን ለማሟላት፤ DCPS፣ በተለይ ደግሞ ቀለም ላላቸው ተማሪዎች (students of color) - የዕድሎችን ክፍተት የሚፈጥሩ ነገሮችን በማጥፋት፣ የተቋማትን የተዛባ አመለካከትን ለማስቀም፣ እና ለቀለም-ትምህርት እና ለማህበራዊ ስኬቶች እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች የሚያስወግድ አካባቢን በመፍጠር ላይ ትኩረት ያደርጋል። ከአድልዎ ነፃ የሆነ - እኩልነት ያለው አካባቢን ለማቅረብ፤ በተለይ የበለጠ የመለያየት ልዩነቶች በሚታዩባቸው ነገሮች ላይ የበለጠ እርዳታዎችን በመስጠት፤ የማግኘት ዕድል፣ አብሮ-መካተትን (inclusion)፣ እና ማረጋገጫን፤ DCPS የሚሰጥ ይሆናል። DCPS በተጨማሪም፣ ለሠራተኞች እና ጎብኚ-እንግዶች፤ ከአድልዎ-ነፃ የሆነ አካባቢን ለመስጠት በቁርጠርኝነት ይሠራል። ጥያቄዎችን ለማስገባት እና አቤቱታዎችን ፋይል ለማድረግ፤ የDCPS አድልዎ-አልባ ማስታወቂያ (Notice of Non-Discrimination) እና የመገኛ-አድራሻ መረጃዎችን፤ በዚህ ማገናኛ ውስጥ ይገኛሉ: https://dcps.dc.gov/non-discrimination።

ይህ ፖሊሲ የሚያሳየው፤ የDCPSን በሁሉም የአድልዎ ዓይነቶች ላይ የሚከለክለውን እና በርካታ የአድልዎ ዓይነቶችን እና ጥበቃ-የተሰጣቸው ባህሪያቶች (protected traits) ላይ የሚወያይ ሲሆን፤ ይህም በተማሪዎች መብቶች ላይ ያተኮረ ነው። ይህ ፖሊሲ፣ ከዚህ ቀደም በዚህ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

## II. ሥልጣን እና በስራ ላይ የሚውል ሕግ[1]

| ምንጭ | ማጣቀሻ (Citation) |
|---|---|
| የፌደራል ሕግ | - አንቀጽ 9 (Title IX) የ1972 የትምህርት ማስተካከያ-የተደረገበት ድንጋጌ (Education Amendments Act)፣ (Title IX), 20 U.S.C. § 1681<br>- የ1973፣ ክፍል 504 መልሶ-ማቋቋም ድንጋጌ (Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973)፣ 29 U.S.C. § 701 *et seq*.<br>- የአንቀጽ 2 (Title II)፣ የ1990 የአሜሪካውያን የጉዳተኝነት ድንጋጌ (Americans with Disabilities Act)፣ 42 U.S.C. § 12101 *et seq*.<br>- አንቀጽ 6 (Title VI)፣ የ1964 የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (Civil Rights Act)፣ 42 U.S.C. § 2000d *et seq*. |
| የፌደራል ደንቦች | - አንቀጽ 9 (Title IX) የማስፈጸሚያ ደንቦች (implementing regulations)፣ 34 C.F.R. Part 106 |
| የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሕግ | - የ1977 የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (DC Human Rights Act)፣ D.C. Code § 2-1401 *et seq*.<br>- የ2004፣ የዲሲ የቋንቋ አገዛ ማግኘት ድንጋጌ (Language Access Act of 2004) D.C. Code § 2-1931 *et seq*.<br>- የ2018፣ የትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ የኦምኒአውቶቡስ/ኦምኒባስ (Omnibus) ማስተካከያ ድንጋጌ (School Safety Omnibus Amendment Act)፣ D.C. Code § 38-951 *et seq*. and D.C. Code § 38-952 *et seq*.<br>- እንዲደረግ-የታዘዘ የሪፖርተር መስፈርቶች (Mandated Reporter Requirements)፣ D.C. Code §4-1501 *et seq*. |
| የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች | - የተማሪ ቅሬታ ሂደቶች (Student Grievance Procedures)፣ 5-B DCMR § 2405<br>- ለወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ እና ጎብኚ-እንግዶች፤ ቅሬታ ሂደቶች (Grievance Procedures for Parents, Guardians, and Visitors)፣ 5-E DCMR § 405 |

[1] Nothing in this policy will supersede federal, state, or local law.

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጉሞች

**ማንጓጠጥ (Bullying)** ማንኛውም ስር-የሰደደ፣ የተስፋፋ ወይም የተደጋገመ ክንውን ወይም ባህሪይ፤ በአካላዊም ሆነ በኤሌክትሮኒክ (electronic) ወይም በቃል (verbal) የተደረገ እና በተገቢው-ሁኔታ የሚከተሉትን ሊያስከትል ይችላል ተብሎ የተገመተውን ያካተተ ማለት ነው:

- ተማሪውን ይሆናል-ተብሎ በሚገመት አስፈሪ የሆነ የአካላዊ ጉዳት በራሳቸው ላይ ወይም በንብረታቸው ላይ ማድረስ፣
- በተማሪው አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ጤንነት ላይ፣ ጉልህ የሆነ የጉዳት-ውጤት የሚያደርስ ነገር መፍጠር፣
- በተማሪው የቀለም-ትምህርት ክንውን ላይ ወይም በትምህርት-ገበታ መገኘት (attendance) ላይ ጉልህ-በሆነ ሁኔታ መስተጓጎልን መፍጠር፣
- በተማሪው የመሳተፍ አቅሙ ላይ ወይም ከትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወይም አገልግሎቶች የሚያገኘውን ጥቅማ-ጥቅሞች ላይ ጉልህ-የሆነ መስተጓጎልን መፍጠር፤ ወይም
- የትምህርት ሂደቱን ወይም የትምህርት ቤት ስዓታዊ አሰራርን፣ በቁሳዊ እና በጉልህ-ሁኔታ ማወክ። (*see* D.C. Code § 2-1535.01)

**ቀለም (Color)** የቆዳ-ቀለም ዓይነት (pigmentation) ወይም የቆዳ-ቀለም (complexion) ማለት ነው።

**በሳይበር ሚንጓጠጥ (Cyberbullying)** ማለት፤ ቴክኖሎጂን ወይም የኤሌክትሮኒክ ዲቫይሶችን - እንደ ስልኮችን፣ የሞባይል ስልኮች (cell phones)፣ ኮምፒውተሮች፣ እና ኢንተርኔትን በመጠቀም ማንጓጠጥ (bullying) ማለት ነው። ይህም የሚያካትተው፤ ነገር-ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ ኢሜል፣ በቀጥታ መልዕክቶችን በመላክ፣ የቴክስት (Text) መልዕክቶች፣ እና በኢንተርኔት ላይ የተለጠፉ-ነገሮች (postings) ናቸው።

**ጉዳተኛነት (Disability)** ማለት፤ በአንድም-ሆነ ከአንድ በላይ በሆነ ዋና የሕይወት ተግባር እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን ከፍተኛ አካላዊም ወይም አዕምሮአዊ እክልን ጉልህ-በሆነ ሁኔታ ውሱንነትን የሚፈጥር ማለት ነው። (D.C. Code § 2-1401.02(5A))

**አድልዎ (Discrimination)** ማለት፤ ኢፍትሃዊ ወይም ጭፍን-ጥላቻ ያለው አቀራረብ ለተለያዩ ምድቦች ያሏቸው ሰዎች ላይ ማድረግ ማለት ነው። አድልዎ (Discrimination) በርካታ ቅርጾችን የያዘ ሊሆን ይችላል፤ ይህም ስድብ-የያዘ ቀልዶች፣ በመጥፎ ስም-መጥራት፣ ማስፈራሪያዎች፣ ማንጓጠጥ፣ የሳይበርማንጓጠጥ (cyberbullying)፣ ወይም ፆታዊ/የአካላዊ ጥቃት በአስተማሪዎች ወይም በተማሪዎች መፈጠርን ያካተተ ነው። ይህን አካትቶ የያዘውም፤ ቃላትን-ያልጨመረ የባህሪይ አገላለጽ፤ እንደ በምስል ወይም በጽሁፍ-ዓረፍተነገሮች ወይም አካላዊ ማስፈራራትን፣ ጉዳት-ማድረስን ወይም ማዋረድን የሚያሳዩ ባህሪያቶች ናቸው። (*see* D.C. Code 2-1401 *et seq.*)

**የቤተሰብ ኃላፊነቶች (Family responsibilities)** ማለት፤ በየግል ግንኙነቶች፤ ይህም የሚያካትተው፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ ልጆችን፣ የልጅ-ልጆችን፣ እና ወላጆችን የሚያግዝ/የሚደግፍ ሰው ማለት ነው። (*see* D.C. Code § 2-1401.02(11A)-(12))

***የፆታ መለያ ወይም ፆታን መግለጫ*** ማለት፤ ከፆታ ጋር ግንኙነት ያለው መለያ፣ ወይም አገላለጽ፣ መግለጫ፣ ወይም የአንድ ግለሰብ ባህሪይ - በትውልድ-ጊዜ የተሰጠን የአንድን-ሰው ፆታ ምንም ሆነ ምን ቢሆን ማለት ነው። (*see* D.C. Code § 2-1401.02(12A))

**የፆታውን-ሁኔታ የማያረጋግጥ (Gender-nonconforming)** ማለት፤ በትውልድ-ጊዜ[2] ከተመደበላቸው ፆታ ጋር፣ የአንድ ሰው የፆታ አገላለጹ - አብዛኛው-ሰው ከሚያምንበት የተለየ የሆነ ማለት ነው።

**ትንኮሳ (Harassment)** ማለት፤ ያልተጋበዘ ወይም ተቀባይነት-የሌለው ፀባይ ማለት ነው።

**ጠበኝነት-ፈጣሪ የሆነ አካባቢ (Hostile Environment)** ማለት፤ ከትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ወይም እንቅስቃሴዎች ከሚገኙ ጥቅማ-ጥቅሞች ወይም ባህሪይው ጉልህ-በሆነ ሁኔታ ከፍተኛነት ያለው፣ ተደጋጋሚ የሆነ፣ ወይም በተስፋፋ-ሁኔታ የሚከለክል ወይም የአንድ ሰው ሊኖረው ከሚችለውን አቅም በማገድ እንዳይካፈል የሚያደርግ አካባቢ ማለት ነው።

**የጋብቻ-ሁኔታ (Marital status)** ማለት፣ በጋብቻ-ውስጥ መሆን፣ ያላገባ፣ በቤት-ውስጥ አብሮ በአጋርነት መኖር፣ ፍቺ፣ መለያየት፣ እና የትዳት ኢጋሩ-በሞት የተለየው (widowed)፤ ማለት ነው። (D.C. Code § 2-1401.02(17))

**የመጡበት አገር (National origin)** ማለት፣ የአንድ ሰው የቀድሞ-የዘር ሃረጉ የመጡበት ሃገር ወይም አካባቢ ማለት ነው።

---

[2] *See* DCPS' Transgender and Gender-Nonconforming Policy Guidance (June 2015).

**የግል አቀራረብ (Personal appearance)** ማለት ውጫዊ-አቀራረብ ሆኖ፤ ነገር ግን፣ በድርጅት የስራ-ቦታ መስፈርትነቶች ላይ ወይም መደበኛነት፤ ተጠያቂነትን ሊያስከት የሚችል አለባበስ ማለት ነው። (D.C. Code § 2-1401.02(22))

**የፖለቲካ ዝንባሌ (Political affiliation)** ማለት፣ ከፖለቲካ ፓርቲ ጋር መመደብ ወይም መደገፍ ማለት ነው። (D.C. Code § 2-1401.02(25))

**ዘር (Race)** ማለት፤ በግል የቀድሞ የዘር ሃረግ ወይም ብሄር ላይ መሠረት ያደረገ፣ የምደባ-ክፍል ወይም የህብረት-ግንኙነትን መፍጠር ማለት ነው።

**ሃይማኖት (Religion)** ማለት፣ ሁሉንም የሃይማኖት አመለካከትን እና ልምምድን፣ እንዲሁም የእምነት ዘዴን፤ መንፈሳዊ-መሆንን ሊያካትት ወይም ላያካትት የሚችል ማለት ነው። (*see* D.C. Code § 2-1401 *et seq.*)

**የበቀል-እርምጃ (Retaliation)** ማለት፤ አንድ ሰው አድልዎን ሪፖርት በማድረጉ፣ በአድልዎ ሁኔታዎች ምርመራ ውስጥ በመካፈል ወይም የአድልዎ እንቅስቃሴን በመቃወሙ ምክንያት፤ (ለምሳሌ፤ አቤቱታዎችን-ማቅረቢያ/petitionን በመፈረም) ማንኛውም ከፍተኛ-የሆነ እርምጃ ከተወሰደበት ማለት ነው።

**ፆታ (Sex)** ማለት፤ የአንድ ሰው ፆታ፣ በፆታ መድልዎ ምክንያት - የሚከተሉትን ባካተተ መልኩ፤ በእርግዝና፣ በልጅ-መውለድ፣ የሕክምና መድሃኒት ጋር በተገናኘ-ሁኔታዎች፣ ጡት-በማጥባት እና በመዋለድ የጤና ውሳኔዎች ላይ መሠረት ያደረገ ወሲባዊ ትንኮሳ (Sexual harassment) እና አድልዎ፣ ማለት ነው። (D.C. Code § 2-1401 *et seq.*)

**ወሲባዊ ግንዛቤ (Sexual orientation)** ማለት፣ በፍቅራዊ-አገላለጽ ወይም በወሲብ - ከአንድ ሰው ጋር ፍላጎት ማሳደር ማለት ነው።[3]

**ሠራተኛ (Staff)** ማለት፤ የትምህርት ቤት ተቀጣሪ-ሠራተኛ ወይም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer)፣ ትምህርት ቤቱ በኮንትራክት በሚሰራበት-አካል ውስጥ ተቀጣሪ-ሠራተኛ፣ ወይም ትምህርት ቤቱ እንደ ወኪል ሆኖ ከትምህርት ቤቱ ጋር በትምህርት ቤቱ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሰሩ፤ ከትምህርት-ቤቱ ጋር በአጋርነት የሚሰራ-አካል ተቀጣሪ-ሠራተኛ ወይም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer) ማለት ነው። (D.C. Code § 38-951.01(5))

**አድብቶ-መከታተል (Stalking)** ማለት፤ በአንድ የተወሰነ-ሰው ላይ አተኩሮ የሚደረግ፣ በዚያ ሰው ላይ በደህንነታቸው ወይም በሌሎች ደህንነት ላይ ፍራቻን በግልጽ በማሳደር፤ ወይም ጉልህ-የሆነ የስሜት ጭንቀትን በመፍጠት የማሰቃየት ባህሪያቶች ውስጥ መሳተፍ ማለት ነው። (*see* D.C. Code § 2-1401.02(29A) and § 22-3133)

**ፆታን-የቀየረ (Transgender)** ማለት፤ የአንድ ሰው የፆታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ ከተለመደውና በትውልዳቸው[4] ጊዜ ከተመደበው ጋር የተለየ የሆነ፣ ማለት ነው።

## IV. መስፈርቶች

### A. የተከለከሉ ባህሪያቶች

DCPS፤ አድልዎን እና ወሲባዊ በደልን በሁሉም ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ጎብኚ-እንግዶች፤ በማንኛውም የDCPS ህንፃ ወይም ፕሮግራም ውስጥ በጥብቅ ይከለክላል። አድልዎ በትዕግስት የሚታይ አይደለም።

DCPS፣ በተቀጣሪ-ሠራተኞች፣ ለቅጥር-አመልካቾች ላይ፣ ወይም ተማሪዎች ላይ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አድልዎ አያደርግም ወይም አድልዎ-ሲደረግ በትዕግስት የሚያልፍ አይሆንም፤ እነዚህም - በእውን ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ወይም በሚታሰብ፤ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት-አመጣጥ፣ በፆታ (እርግዝናን ጨምሮ)፣ በዕድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በአካላዊ ገጽታ፣ በፆታዊ አመለካከት፣ በፆታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰብ ሁኔታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በትምህርት ደረጃ፣ በፖለቲካዊ ዝንባሌ፣ በዘር አመጣጥ (genetic) መረጃ፣ በጉዳተኝነት፣ በገቢ ምንጭ፣ በቤተሰብ ትስስር ውስጥ ባለ ወንጀል ሰለባ መሆን፣ ወይም ደግሞ በመኖሪያ ወይም በንግድ ስፍራ፣ አማካኝነት አድልዎችን ይከለክላል።

---

[3] *See* DCPS' Transgender and Gender-Nonconforming Policy Guidance (June 2015).

[4] *See* DCPS' Transgender and Gender-Nonconforming Policy Guidance (June 2015).

DCPS በተጨማሪም፣ በማንኛውም ጥበቃ በተደረገበት ባህሪይ ላይ ትኮሳን (harassment) እና አድልዎን ሪፖርት በማድረጉ ምክንያት፣ በአንድ ሰው ላይ የሚደረግ የበቀል-እርምጃን በአድልዎ ላይ ክስ-መቅረብን ወይም በአድልዎ ምርመራ ወይም የህግ-ክስ ውስጥ መካፈል ላይ መሠረት በማድረግ-የሚከለክል ነው። ተቀጣሪ-ሠራተኞች፤ በተከለከለው አድልዎ፣ ትንኮሳ፣ ወይም የበቀል-እርምጃን ውስጥ ሲሳተፉ ቢገኙ፣ ለስነምግባር መቅጫ የሚዳርጋቸው ይሆናል።

አድልዎ እና ትንኮሳ (harassment)፤ የሚከተሉትን ጨምሮ - በሁሉን-ዓይነት አቀራረባቸው የተከለከሉ ናቸው:

- ማንጓጠጥ (Bullying)፣
- የሳይበር-ማንጓጠጥ (Cyberbullying)፣
- አድብቶ-መከታተል (Stalking)፣
- የዲሲ የ2004 በቋንቋ አገዛ ማግኛ ድንጋጌ (DC Language Access Act of 2004) ጥሰቶች፣
- በዘር፣ በቀለም፣ በዜግነት-አመጣጥ፣ በጉዳተኝነት፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በአካላዊ ገጽታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በፖለቲካ ዝንባሌ፣ በፆታዊ አመለካከት፣ በፆታ መለያ ወይም በፆታ አገላለጽ (ፆታን-የቀየረ/transgender፣ በመቀየር ላይ የሚገኝ እና የፆታውን-ሁኔታ የማያረጋግጥ/gender-nonconforming የሆነን ሰው ጨምሮ)፤ ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ ጭፍን-የሆነ ጥላቻን ማሳየት፣
- ተመራጭ-በሆነውን የስም መጠሪያዎች ወይም ተውላጠ-ስሞች (pronouns)ን፣ ሆን-ብሎ አለመጠቀም፤
- ወላጅነትን እያከናወነ ያለን ሰው፣ ነፍሰ-ጡርን፣ ወይም ጡት-የሚያጠቡን፤ ጭፍን-የሆነ ጥላቻን ማሳየት፣
- ተገቢ-ያልሆነ እና እኩልነት የሌለው የአለባበስ-ኮድ በስራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣
- አንድን ሰው በአትሌቲክ እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ በመጸዳጃ-ቤቶች፣ ወይም በተቋሞች ውስጥ፣ ባላቸው የጾታ ሁኔታ ላይ ወይም የፆታ መለያ ላይ መሠረት በማድረግ፣ እንዳይጠቀሙ መከልከል፤ እና የበቀል-እርምጃ መውሰድ።

ፆታዊ በደል (Sexual misconduct)[5]፤ በሁሉም አቀማመጦች ውስጥ የተከለከሉ ሲሆኑ፣ የሚከተሉትንም ያካትታሉ:

- በፍቅር-ጓደኝነት ጊዜ (Dating) ጥቃት፣
- የቤት ውስጥ ጥቃት (Domestic Violence)፣
- ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱን በመጠቀም የወሲብ ጥቃት መፈጸም፣
- ስምምነት ያልተደረበት (Non-consensual) የወሲብ ምስሎች (pornography)
- ወሲባዊ ትንኮሳ (Sexual harassment)፣
- ወሲባዊ ጉዳት (Sexual abuse)፣
- ወሲባዊ ጥቃት (Sexual assault)
- አድብቶ-መከታተል (Stalking)
- እርዳታን፣ ጥቅማ-ጥቅምን ወይም አገልግሎትን - አንድን-ግለሰብ ከሚሳተፍበት አቅርቦት፤ ተቀባይነት-በሌለው የወሲባዊ ባህሪይ ካልተሳተፉ፣ እንዳያገኙ መከልከል (ማለትም፤ የ'ኩዊድ ፕሮ ኮ/quid pro quo' ትንኮሳ)፤ እና
- ተቀባይነት የሌለው ባህሪይ።

1. በዘር፣ በቀለም፣ ወይም በሃገር ተወላጅነት መነሻ ላይ መሠረት ያደረገ፣ አድልዎ ማድረግ

DCPS፤ በዘር፣ በቀለም፣ ወይም በሃገር ተወላጅነት ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎ ማድረግን፣ በትዕግስት የሚመለከተው አይሆንም። በዘር፣ በቀለም፣ ወይም በሃገር ተወላጅነት መነሻ ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎ፤ በማንኛውም በአንድ ግለሰብ ላይ የሚደረግ በሚከተሉትን ላይ ያተኮረ አድልዎ ነው:

- የሰውየው የቀድሞ የዘር-ሃረግ የመጣበት ቦታ ወይም የመጣበት ነው-ተብሎ በተወሰደው፣ የአለም ክልል፣ ወይም ሃገር፤
- የአንድን ሰው የኢሚግሬሽን ወይም የዜግነት ሁኔታ፣
- የአንድ ሰውን የቆዳ-ቀለም፤ በአንድ-ሰው የተለየ የቆዳ ቀለም ዓይነት ምክንያት በተለየ-ሁኔታ ማስተናገድን ጨምሮ፤
- በአንድ ሰው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ-ውሱንነት ወይም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪ በመሆኑ ምክንያት፣ ወይም

[5] For more information, please see DCPS policies on *Preventing and Addressing Student-on-Student Acts of Sexual Misconduct* and *Prevention of Student Sexual Abuse by Staff* at https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

- የአንድ-ሰው በእውን ያለው ወይም ይሆናል ተብሎ የሚገመተው የቀድሞ-የዘር ሃረጉ ወይም ጎሣዊ ባህሪያቶቹ፤ ይህም የሚያካትተው - የሃይማኖት አባልነቱ፣ (እንደ፣ ሂንዱ/ Hindu፣ ጁዊሽ/Jewish፣ ሙስሊም/Muslim፣ እና ሲክ/Sikh የሆኑ ግለሰቦች) ይህንን ባህሪያቶች ሊያሳይ የሚችል ሆነው ሲወሰዱ።

በዘር፣ በቀለም፣ ወይም በሃገር ተወላጅነት መነሻ ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎ፤ ብዙ ቅርፆችን ሊይዝ የሚችል ሲሆን፤ ይህም የሚያካትተው በጎሣ ወይም በቀድሞ የዘር ሃረግ ላይ የሚደርስ-ስድቦች፣ ባላቸው-አመለካከት የሚፀኑ (stereotypes)፣ ወይም አላግባብ-የሆነ ስም መጥራት ሊያካትቱ ይችላሉ። ግለሰቦች ባላቸው ገጽታቸው - በደል ሊደርስባቸው ይችላል፤ (ይህም ባላቸው ገጽታዎች ሲሆን)፣ በአለባበስ፣ የአነጋገር መንገዶቻቸው፣ ከዘር ወይም የቀድሞ የዘር ሃረግ አመጣጥ ጋር እንዲገናኝ በማድረግ ሊሆን ይችላል። ይህም ሊያካትት የሚችለው፣ በዘር ላይ ያተኮረ ማስፈራሪያዎች፣ ጥቃቶች፣ ወይም ሌላ የጥላቻ ባህሪይ ናቸው።

ከዘረኝነት-ነፃ የሆነ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት እንደመሆኑ፤ DCPS፣ ስልታዊ ዘረኝነት እና የተወሰኑ-ክፍሎችን ከፋፍሎ የመጨቆን አሰራርን እስከመጨረሻው ለማጥፋት በቁርጠኝነት ይሠራል። የDCPS ሠራተኞች፤ **የራስን-ማንነት መለየት እና አስተሳሰቦችን** እና **ልምድን፤** በማዳበር፣ እንዲሁም የጋራ-የሆነ **ባህልን** እና ***ፖሊሲን በመቅረጽ***፤ ከዘረኝነት-ነፃ ወደ-ሆነ መንገድ ግለሰቦችን ለማሸጋገር በቁርጠኝነት ይሠራሉ። DCPS፣ የግል እና ተቋማዊ የዘር እኩልነትን የሚያሳጡ ነገሮችን ለመዋጋት፤ በማወቅ እና ሆን-ተብሎ የተደረጉ እርምጃዎችን በመጠቀም፤ ሁሉም ተማሪዎች - ጥራት ያለው ትምህርት፣ የመረጃ-ምንጮችን (resources)፣ እርዳታን፣ እና ፕሮግራሞችን ማግኘታቸው በማረጋገጥ፤ በቁርጠኝነት ይሠራል። DCPS፤ በተለይ የበለጠ የመለያየት ልዩነቶች በሚታዩባቸው ነገሮች ላይ የበለጠ እርዳታዎችን በመስጠት፤ የማግኘት ዕድል፣ አብሮ-መካተትን (inclusion)፣ እና ማረጋገጫን በመስጠት ይሠራል። DCPS፤ በስርዓተ-ትምህርት እድገት፣ ፈተና፣ ስነምግባር፣ የሠራተኛ የእርስ-በእርስ ግንኙነት፣ እና ከጉዳተኝነት (Disabilities) ጋር የሚገኙ ተማሪዎችን በመለየት ላይ ያሉትን ልዩነቶች፣ መፍትሄ ለመስጠት ይሠራል። የማህበራዊ-ስሜታዊነት መማርን፣ በባህላዊነት-ምላሽ የሚሰጡ ልምዶችን በአንድ-ላይ በማቀናጀት፣ እና ቀጣይነት ያለውን ከዘነኝነት ነፃ የሆነ የሙያ ማሳደጊያ (professional development) ለሠራተኞች በመስጠት፤ DCPS፣ ሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች የመወደድ ስሜት እንዲኖራቸው፣ የተቀባይነት-ስሜት፣ ፈታኝ-ነገሮችን መቋቋም እና ለእየዕለቱ ክንውን ዝግጁነት እንዲሰማቸው ያረጋግጣል።

2. በፆታ፣ ፆታዊ ግንዛቤ፣ በፆታ መለያቸው፣ ወይም አገላለጽ[6] ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎ፤

DCPS፣ በፆታ፣ ፆታዊ ግንዛቤ፣ በፆታ መለያቸው፣ ወይም በፆታ አገላለጽ ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎን፤ በትዕግስት-እየተመለከተ የሚያልፈው አይደለም። በፆታዊ ግንዛቤ ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎ፣ የሚወስደው ወደ ግብረ-ሰዶማዊ (homophobic) አባባሎች፣ የፆታ ግንዛቤ ላይ መሠረት ያደረገ ትንኮሳን፣ ወይም ጥሰትን[7] ያስከተለ ሊሆን ይችላል። አድልዎው የሚያካትተው፤ በእርግዝና፣ በልጅ-መወለድ፣ በሕክምና ሁኔታ ጋር ግንኙነት ባላቸው ነገሮች፣ በጡት-ማጥባት፣ ወይም በመዋለጃ-ጤና ውሳኔያቸው[8] ላይ የሚኖርን መድልዎ ያካተተ ይሆናል።

a. አትሌቲክስ (Athletics)

ሁሉም የአትሌቲክስ ፕሮግራሞች፤ እኩል የሆነ-ዕድሎዎችን፣ ለሁሉም ተማሪዎች ማቅረብ አለባቸው። ተማሪዎች በእንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ እንደ 'በintramural እና interscholastic አትሌቲክሶች ያሉ፣ ከየፆታ መለያቸው ጋር ተደጋጋሚ በሆነ መልኩ በሚሰጡ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲካፈሉ መፈቀድ አለበት።

b. ጡት-ማጥባት (Breastfeeding)

ተማሪዎች ለልጃቸው በማንኛውም ቦታ፣ የሕዝብ ወይም የግል፣ በማንኛውም ከልጃቸው ጋር የመሆን እና የወላጅን-ጡት ወይም ማንኛውም የሰውነት-ክፍል ሳይሸፈን በዚህ-ሁኔታ በሚካሄድበት ጊዜ ወይም ልጃቸውን ጡት-በሚያጠቡ ጊዜ መብት በሚሰጣቸው ቦታ፤ ጡት-የማጥባት መብት አላቸው። DCPS፤ ከጡት-ማጥባት ጋር በተያያዘ የተከሰቱ ከክፍል መቅረቶች ምክንያት ያመለጧቸውን ማንኛውም ስራዎችን፤ በሚችሉት-ጊዜ ሰርተው እንዲያካክሱ ዕድሎችን ለተማሪዎች መስጠት አለበት።

[6] For more information on students who are transitioning, please see the DCPS Transgender and Gender-Nonconforming Policy Guidance or the DCPS LBGTQ family guide. Both documents contain resources including a school planning tool that can support students as they transition.

[7] For more information, please see the DCPS Transgender and Gender-Nonconforming Policy Guidance or the DCPS LBGTQ family guide. Both documents contain resources including a school planning tool that can support students as they transition.

[8] *See* D.C. Code § 2-1401.05(a).

c. የአለባበስ ኮዶች

ተማሪዎች፣ እንደየፆታቸው መለያ፤ የትምህርት ቤቱ የአለባበስ ኮድ በሚፈቅደው-ደንቦች ውስጥ በሆነ የመልበስ መብት ያላቸው፣ እና የአለባበስ ኮዶቹ፣ ለሁሉም ተማሪዎች - የፆታ ሁኔታቸው ወይም ማንኛውም የአካላዊ ባህሪያት ምንም-ሆነ ምን፤ በእኩልነት እና ሁሉንም-ባካተተ መልኩ መተግበር አለበት። በተጨማሪም፤ የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ በግል-ስሜት ወይም በግል-የተማሪው የአለባበስ ምርጫ ላይ (ለምሳሌ፤ የተማሪው ሱሪ "በጣም ጠባብ/too tight" መሆኑን ሠራተኛው አስተያየት መስጠት) ባለው-ሁኔታ ጫና-መፍጠር አይችሉም። በአለባበስ ኮድ ጥሰቶች የተከሰሰ ማንም ሰው፤ በምንም-ዓይነት ሁኔታ - የትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ ማስወገድን (suspensions) ወይም-ደግሞ ከክፍል ውስጥ የሚወጣበት፣ ወይም ወደ ትምህርት ቤት ወይም ከትምህርት-በኋላ እንቅስቃሴዎች ወይም ፕሮግራሞች ውስጥ እንዳይካፈል የሚከለክል ቅጣት ሊደርስበት አይችልም። የትምህርት ቤት የአለባበስ ኮዶች፣ ከፆታ-ገለልተኛ መሆን አለባቸው። ለምሳሌ፤ ትምህርት ቤቶች፣ "ሴት-ልጆች ጉርድ-ቀሚሶችን እንዲያደርጉ" መጠየቅ አይችሉም። ይህም በስራ-ላይ የሚውለው፤ በመደበኛ የትምህርት ቀናቶች እና በተጨማሪም በልዩ-ዝግጅቶች በሆኑት - እንደ ፕሮም (prom) ባሉትም-ጊዜያቶች ውስጥም ይሆናል።

d. ስሞች እና ተውላጠ-ስሞች (Pronouns)

ከፆታ-መለያቸው ጋር በሚሄድ ሁኔታ፣ ተማሪዎች በስማቸው እና በተውላጠ-ስም የመጠራት መብት አላቸው። ከፍርድ ቤት የታዘዘ የስም ወይም የፆታ መቀየሪያ አያስፈልግም፤ እና ተማሪዎች ይፋ-የሆነውን መዝገባቸውን መቀየር አያስፈልጋቸውም። ተማሪው በሚመርጠው ስም ወይም ተውላጠ-ስም ሆን-ብሎ አለመጥራት፣ በስነምግባት መቅጫ ሊያስጠይቅ ይችላል።

e. ነፍሰ-ጡር/በወላጅነት ተሞክሮ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች

ነፍሰ-ጡር የሆኑ ተማሪዎች፣ በክፍል-ውስጥ እና ከትምህርት-ቤት ውጪ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፋቸው እንዲቀጥሉ መፈቀድ አለበት። ነፍሰ-ጡር የሆኑ ተማሪዎች፣ በልዩ የትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራሞች ውስጥ ወይም ለእርጉዝ ተማሪዎች የሚሰጡ ክፍለ-ጊዜዎች ውስጥ ለመካፈል መፈለግ-ወይም አለመፈለጋቸውን እንዲመርጡ፣ DCPS ሊፈቅድላቸው ይገባል። ተማሪዎች እነዚህም ውሳኔዎች፣ ከDCPS ሠራተኞች ምንም-ጫና ሳይደረግባቸው በራሳቸው እንዲወስኑ መፍቀድ አለበት። ማንኛውም አማራጭ ፕሮግራሞች፤ አንድ ዓይነት የሆኑ የቀለም ትምህርት ፕሮግራም-አሰጣጥን እና፣ በስራ-ላይ በሚውሉ፣ በልዩ ትምህርት እና በተያያዥ አገልግሎቶች ውስጥም ቢሆን፣ ልክ-እንደ ትምህርት ቤቱ መደበኛ ፕሮግራም መሰጠት አለበት። ለሁሉም ተሳታፊ ተማሪዎች የሐኪም ወረቀት ማስገባት እስካላስፈለገ ድረስ፤ ነፍሰ-ጡር የሆኑ ተማሪዎች፣ በእንቅስቃሴዎች ውስጥ ለመሳተፍ፣ የሐኪም ወረቀት እንዲያስገቡ መጠየቅ የለባቸውም። DCPS፣ እንደ የመቀመጫ ወይም የዴስክ (desk) ማስተካከያዎች፣ የሊፍት-አሳንሰር (elevator) ማግኘት፣ ወይም አስፈላጊ-በሚሆን ጊዜ እና ከእርግዝና-ጋር በተያያዘ ወደ መታጠቢያ-ቤት ቶሎ-ቶሎ የመሄድ ማመቻቻዎችን፤ በተገቢው-ሁኔታ ማስተካከያዎችን ማድረግ አለበት። DCPS፤ ከእርግዝና ጋር በተያያዘ የተከሰቱ መቅረቶች-ምክንያት ያመለጧቸውን ማንኛውም ስራዎችን፤ በሚችሉት-ጊዜ ሰርተው እንዲያካክሱ ዕድሎችን ለተማሪዎች መስጠት አለበት።

f. መጸዳጃ-ቤቶች/ተቋማት

ተማሪዎች፣ ደህንነቱ-በተጠበቀ ሁኔታ የመጸዳጃ ቤቶችን እና ተቋማቶችን በፆታቸው መለያ በሚስማማ መልኩ፣ መጠቀም መቻል መብት አላቸው። ተማሪዎች፣ አማራጭ ማመቻቻዎችን እስካልጠየቁ በቀር፤ ሌሎች እኩዮቻቸው የሚጠቀሙትን የመታጠቢያ-ቤቶች መጠቀም ይችላሉ። ፆታን-የቀየረ (Transgender) ወይም የፆታውን-ሁኔታ የማያረጋግጥ (non-conforming) ተማሪዎች፤ እንደ-ብቸኛ አማራጫቸው ሆኖ፣ የአንድ-ሰው ጥቅም ብቻ በሚያገለግል የመታጠቢያ ቤቶች (bathrooms) ውስጥ እንዲጠቀሙ መገደድ የለባቸውም።

3. በጉዳተኝነት ላይ መሠረት ያደረገ፣ አድልዎ

DCPS፣ በጉዳተኝነት ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎን በትዕግስት የሚያልፈው ነገር አይደለም። ማንኛውም ባህሪይ - በአንድ ግለሰብ በእውን-ባለው ወይም ሊኖረው-ይችላል በሚባል ጉዳተኝነት[9] ምክንያት፣ በጉዳተኝነት ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎ ይባላል። የጉዳተኝነት አድልዎ፣ ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች ሊያገኙ በሚችሉት፣ የቀለም ትምህርት እድገታቸው ወሳኝ የሆነ ትምህርት ላይ - ሊፃረር

[9] DCPS is required to provide students with disabilities a free and appropriate public education (FAPE) under the Individuals with Disabilities Education Act (IDEA). For more information regarding IDEA at DCPS, please see the Division of Specialized Instruction Resource Guide. Information the Section 504 program can be found at https://dcps.dc.gov/page/section-504.

የሚችል እና፣ ነፃ እና ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርትን ለመከልከል የሚዳርግ ሊሆን ይችላል። የጉዳተኝነት አድልዎ ሊያካትታቸው የሚችለው ምሳሌዎች፤ ማቃለል (belittling) ወይም የተማሪውን የምሁራዊ ጉዳተኝነትን መተቸት ወይም የተማሪውን ዊልቼር (wheelchair) መሄጃ መንገድ ላይ እንቅፋት ማድረግ ናቸው።

4. በቋንቋ ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ላይ መሠረት ያደርገ አድልዎ

DCPS፤ በቋንቋ ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ የችሎታ-ብቃት ላይ መሠረት ያደረገን አድልዎ በትዕግስት የሚመለከተው አይሆንም። DCPS፤ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ለመናገር፣ ለማንበብ፣ ወይም ለመፃፍ ውስን እውቀት ያላቸው ወይም የማይችሉ - በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ ነዋሪዎችን፤ በሕዝብ አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች፣ እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ በእኩልነት-የማግኘት እና የመካፈል መብት ይሰጣል[10]። አንድ-ሰው ወደ DCPS ግንኙነት ካደረገ እና መናገር፣ ማንበብ፣ መፃፍ፣ ወይም እንግሊዘኛ ቋንቋን መገንዘብ ካልቻሉ፤ የሚከተሉትን ለማግኘት መብት አላቸው:

- የማስተርጎም-አገልግሎቶችን ካለምንም-ክፍያ መጠየቅ እና ማግኘት፣
- ወሳኝ-የሆኑ ሰነዶችን፣ በሚናገሩት ቋንቋ ካለምንም-ክፍያ ለማግኘት መጠየቅ እና ማግኘት፣ እና
- አገልግሎቱን እንዳያገኙ ከተከለከሉ፣ አቤቱታዎችን እንዲያደርጉ።

## B. በተከለከሉ ባህሪያቶች ላይ የሚደረጉ ምርመራዎች እና የሚያስከትሉት-ውጤቶች

DCPS፤ ፀረ-መድልዎ የሚታይበትን-አካባቢን መፍጠር የሚያስፈልገው እና እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በሚፈጠሩ ጊዜም፣ መፍትሄዎችን ማቅረብ አለበት። ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ወይም የትምህርት ቤት ኅብረ-እንግዶች፤ በተከለከለ-ባህሪይ (prohibited behavior) ወይም በበቀል-ተግባር ውስጥ በመካፈል ከተከሰሱ፤ የDCPS፣ 'Comprehensive Alternative Resolution & Equity (CARE)' ቡድን፣ በአሁኑ በDCPS የቅሬታ ፖሊሲዎች[11] ዝርዝሮች ውስጥ ያሉትን የምርመራውን ሂደቶች ይከተላል። ጥሰቱ መደረጉ-ከተገኘ፣ በዚያ ፖሊሲ አማካኝነት የሚከናወኑ እና በሁሉም ተገቢ-በሆኑ የአካባቢ እና የፌደራል ሕግ እና ደንቦች በሚያስከትሉት-ውጤቶች (consequences) መሠረት ይከናወናል። በምርመራ እና በመፍትሄ መስጠት አማካኝነት፤ ማንኛውንም የተበሳጨውን-ቡድን፣ በሙሉነት እና ስልታዊ ውድቀቶች ላይ መፍትሄ ለመስጠት የ'DCPS CARE' ቡድን ይጠይቃል። መፍትሄ-መስጠቶች፤ በፖሊሲ ለውጦች፣ በአገልግሎት ድንጋጌ፣ እና/ወይም ከመልስ-ሰጪው ጋር በሚኖር የስነምግባር እርምጃን ሊያስከትል ይችላል። የስነምግባር እርምጃ፣ ከDCPS የተማሪ የስነምግባር ፖሊሲዎች[112] ጋር በተያያዘ የሚከናወን ይሆናል።

## C. መከላከል (Prevention)

በትምህርት ቤታችን ውስጥ፣ የመከላከልን እና በንቃት በመድልዎ ላይ የሚደረጉ ነገሮች ላይ መፍትሄ በመስጠት፤ አስፈላጊነት ያለውን-ቦታ በመስጠት፣ DCPS የሚከተሉትን ያደርጋል:

- ሁሉም ተማሪዎች፣ የመወደድ ስሜት፣ ፈተናን ተቋቋሚነት፣ እና የዝግጁነት ስሜት የሚሰማቸውን አካባቢ መፍጠር፣
- ቀጣይነት ያለው የፀረ-ዘረኝነት፣ ፀረ-መድልዎ ስልጠናን ለDCPS ሠራተኞች መስጠት፣
- ማህበራዊ-ስሜታዊነት የሙያ-ማሳደጊያ (professional development)ን ለDCPS ሠራተኞች መስጠት፣
- በባህላዊ ምላሽ መስጠት ትምህርት እና ልምምዶች ዙሪያ የሙያ-ማሳደጊያ (professional development)ን ለDCPS ሠራተኞች መስጠት፣
- በትምህርት ቤቶች ውስጥ እና በሌሎች የDCPS ቦታዎች ውስጥ፣ ፀረ-መድልዎ እና ትንኮሳ (harassment) ፕሮግራሞችን እና እንቅስቃሴዎችን ማካተት፣
- ተማሪዎችን፣ እንክብካቤ-ሰጪዎችን፣ እና የትምህርት ቤት ኅብረ-እንግዶችን፣ መድልዎ እና ትንኮሳ (harassment)ን ሪፖርት እንዲያደርጉ ማበረታታት፣
- የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ መድልዎ እና ትንኮሳ (harassment)ን ሪፖርት እንዲያደርጉ አስፈላጊ-ማድረግ፣
- የተደረገበት ምክንያት ምንም-ሆነ ምን፣ በጥላቻ እና በተዛባ-አመለካከት ላይ የሚከሰቱ ነገሮች ላይ ምላሽ መስጠትን በዲስትሪክት-አቀፍ ፕሮቶኮል ማስፈጸም፣ እና
- መድልዎ የሚከናወንበር አካባቢዎ ካሉ ለመወሰን እና እንደ-የተገቢነቱ ምላሽ ለመስጠት፤ የአካባቢውን ሁኔታ ግምገማ ማድረጊያዎችን ማከናወን።

---

[10] Language Access Act of 2004, D.C. Code § 2-1931 *et seq*. For more information on the Language Access Act of 2004, please visit https://dcps.dc.gov/node/1513801.

[11] Available at https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

[12] *Available at* https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

### D. የመረጃ-ምንጮች (Resources)

DCPS፤ የአድልዎ አቤቱታን መልስ ለመስጠት እና ለመርዳት የሚገኝ፣ እና የDCPS የፍርሃዊ-እኩልነት ስልት እና የፕሮግራም አሰራር ቡድን ደግሞ፣ የዕድሎች ክፍተቶችን በማጥፋት፣ ተቋማዊ-የተዛባ አመለካከትን የሚያስቆም እና በቀለም ትምህርት እና በማህበራዊ ስኬቶች ላይ እንቅፋቶችን የሚያስወግድ አካባቢን ለመፍጠት DCPS ይሰራል። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት በተጨማሪም፤ አድሎአዊ አሰራር የደረሰባቸውን ተማሪዎች ለመርዳት፣ የማህበራዊ ሠራተኛ (social worker)/የአዕምሮ ጤና ቡድን ያሉት እና የማህበራዊ የመረጃ-ምንጮችን (resources) በመለየት ይረዳሉ። በተጨማሪም፤ የቀለም-ትምህርት እርዳታ (ለምሳሌ፤ ማስጠናት) ለተማሪዎች የአድልዎ ወይም የጥቃት ሁኔታዎችን ምሳሌ አድርጎ በተከተለ ሁኔታ የሚገኝ ይሆናል።

## V. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚፈለጉ መስፈርቶች

ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች፤ በዚህ በተቀረጸው ፖሊሲ መስፈርቶች መገዛት ያስፈልጋቸዋል። የዚህ ፖሊሲ የማስፈጸም ህግ የሚጠበቀው፤ በፀረ-መድልዎ (anti-discrimination)፣ የአንቀጽ 9 (Title IX)፣ እና የተስተካከለው የሪፖርተር ስልጠናዎች፤ ለሠራተኛ የተሰጠው እንዲሁም በቀጣይነት ቁጥጥር እየተደረገበት በ'DCPS Care' ቡድን በሚታየው ይሆናል። ስልጠናዎቹ፤ አድልዎን እንዴት እንደሚገልጹ እና ከአድልዎ ነፃ የሆነ አካባቢን ለመፍጠር እና የሠራተኛውን ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነቶች ላይ ይወያያል።

DCPS እያንዳንዱን ተማሪ፤ በፍህታዊነት፣ የላቀ-በላጭነት፣ ግልጽነት፣ እና ተጠያቂነት ባለው-ሁኔታ ለማገልገል ቁርጠኝነቱን የሚያሳይ እና ለተማሪዎች የአድልዎ እና ከጥቃት-ነፃ የሆነ አካባቢን መፍጠር ነው። በዚህ ፖሊሲ ላይ እና አፈጻጸሙን በተመለከተ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉ፣ ወደ 'DCPS CARE' ቡድን፣ በdcps.care@k12.dc.gov ሊላኩ ይገባል። ስለ ተጨማሪ-ስጋቶች ወይም በዚህ ትዕዛዛት ላይ ጥሰቶችን ለማሳወቅ፤ ይህን ትዕዛዝ መስጫ፣ የሃቀኝነት ሹሙ ዋና የሆነው (Chief Integrity Officer)ን ለማነጋገር፤ የኦንላይን-መምሪያ (Online Referral) ቅጽን[13] በመሙላት ወይም ወደ dcps.cio@k12.dc.gov ኢሜል መላክ።

የእንባ-ጠባቂ ቢሮ (The Office of the Ombudsman)፤ በቅሬታዎች ውስጥ-ለተካተቱ ተማሪዎች፣ እንደ አማካሪ-ሆኖ ሊያገለግል ይችል ይሆናል። ለተጨማሪ መረጃ፣ https://sboe.dc.gov/page/office-of-the-ombudsman-for-public-education ተመልከቱ ወይም የሚከተለውን ያነጋግሩ:

የስቴት የትምህርት ቦርድ (State Board of Education)
Office of the Ombudsman for Public Education
One Judiciary Square
441 4th Street, NW, 530S
Washington, DC 20001
ስልክ: (202) 741-0886
ኢሜል: education.ombudsman@dc.gov

[13] *Available at* https://dcps.dc.gov/page/office-integrity.